# በስመ አብ ወወልድ

# ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

# አሜን::

# ዘፍን፣ ጭፈራና ተጽእኖው

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
የካቲት ፬ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# መግቢያ

- ብናምንም ባናምንም በርካታዎች በተለያዩ የሙዚቃ ዓይነቶች ተጽእኖ ሥር የወደቅን ነን፡፡ (Jazz, Blues, Rock and Roll, Rhythm and Blues, Country and Western, Hip Hop, Classical…)

- እግዚአብሔር ዜማን የሰጠን በመንፈሳዊነት የሚመራ ልባችንን እንድንሰማበት ነው፡፡

- ዜማ ነፍስን ለማበርታት፤ አእምሮን ከክፉ ለማሻገርና ለማስደሰት፤ ለፍርሐታችን ጸጥታ በመሆን ሰላምንና ፍቅርን ማስተላለፊያ ሊሆን ይችላል፡፡

- ዜማን በተሳሳተ መንገድ ከተጠቀምንበት ግን አእምሮን ሊያበላሽ፤ ወደ ኃጢአት ሊመራ፤ ሁከተኛ፤ ተገቢ ላልሆነ አለባበስ፤ እርስ በርስ ለመናናቅ፤ ዘመናችንን በእስር ቤት እንድንጨርስ የሚያደርጉ የሞኝነት ወንጀሎችን ለመፈጸም፤ ወይም እስከሞትም ለሚያደርስ ወንጀል ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

- የዛሬውም ትምህርት ማዕከሉ ይኸው ነው፡፡

- ሶስቱ ወጣቶች ሲድራቅ ሚሳቅና አብደናጎ ናቡከደነፆር ላሰራው ምስል የዘፈኑን ድምጽ ሲሰሙ ይሰግዱ ዘንድ ቢታዘዙም ትዕዛዙን አልተቀበሉትም፡፡

# ዘፈንና ዳንስ በመጽሐፍ ቅዱስ

- ቅዱስ መጽሐፍ ዘፈንን በሁለት መንገድ ያስቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ንጉሥ ዳዊት፤ የሙሴ እህት ማርያምና ሌሎችም ያቀረቡትን ማኅሌታዊ አገልግሎት 2ኛ ሳሙ. 6:14 እና ዘጸአት 15:20 የሚመለከት ሲሆን

- ሁለተኛው እንደ ሄሮድያዳ ልጅ ራስን ለሌላው ለማሳየት ማቴ 14:6 ወይም ከሥነምግባር በወጣ ድርጊት የሚፈጸም ነው፡፡ ዘጸአት 32:19 -25፡፡ ዳንስ ወይም ጭፈራ ንጉሡን የቅዱስ ዮሐንስን አንገት ቆርጦ እንዲያቀርብ አደፋፍሮታል፡፡ ማቴ 14:1-2፤ ማር 6:14-29፤ ሉቃስ 9:7-9

- አዲስ ኪዳን ስለ ዓለማዊው ዘፈንና ዳንስ በሮሜ 12:1-21፤ 1ኛ ዮሐ. 2:15-17፤ ገላትያ 5:19-21 ተናግ[ል፡፡ ይኽ ስሜታዊ፤ ሥጋዊና ዓለማዊ እንደሆነ ከመግለጽ በተጨማሪ ሰውነታቸውን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡትን የማይመለከትና ከኃጢአት ድርጊቶች ጋር ተስማሚነት ያለው መሆኑን አስረድቷል፡፡

- የሥጋ ፈቃድን የማነሳሳት አቅጣጫ ካለው በማንኛውም ዓይነት ልቅ የሥጋ ጭፈራ ከመሳተፍ መቆጠብ ይገባናል፡፡ ገላትያ 5:19-21፡፡

# ዘፈንና ዳንስ በመጽሐፍ ቅዱስ የቀጠለ...

- ሰውነትን በማነካካት ወይም ለፍትወት በማነሳሳት የሚከናወኑ እንደ ሮክ ያሉ ሙዚቃዎች በሁለቱም ጾታ መጥፎ ስሜትን ይቀሰቅሳሉ፡፡ ቅዱስ ጳውሉስ ወጣቱ ጢሞቴዎስን #ራስህን በንጽሕና ጠብቅ; 1ኛ ጢሞ 5፡22 ጠቢቡ ሰሎሞንም #አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና; ምሳሌ 4፡23፤ 23፡7 በማለት ይመክራሉ፡፡

- ጌታችንም ኃጢአት በአካላችን ወይም በሰውነታችን የሚፈጸም ብቻ ሳይሆን በልብ የሚጀምር መሆኑን አስተምሮናል፡፡ #እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፡፡; ማቴ 5፡28 ወደ ፈተና አታግባን ብለን የምንጸልየው ለዚሁ ነው፡፡ ማቴ 6፡13፡፡

- በየት/ቤቶቹ ያሉ ጭፈራዎችና ዳንሶች የአንድን ሰው ጠባይ የማበላሸት አቅም አላቸው፡፡ እኛ ንጽሕናችንን በመጠበቅ ንጹሕ ለሆነ ነገር ብቻ የቆምን የዓለም ብርሃን መሆናችንን ሌሎችም እንዲያውቁልን በማድረግ እርምጃችንን እንጠብቅ፡፡ ማቴ 5፡14-16፤ ፊል 2፡15-16

- ጭፈራና ዳንስ በብዙዎች ወደ ተጨናነቁና ጭፈራን፤ መጠጥንና ስካርን በሚወዱ ሰዎች መካከል የተሳሳተ ቦታ ላይ ሊጥል ይችላል፡፡

# ዘፈንና ዳንስ በመጽሐፍ ቅዱስ የቀጠለ...

- ሌሎች ሲጨፍሩ ቢያዩም ክፉ ነገር የማያስቡ ስለመሆናቸው የሚከራከሩ ወጣቶች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን ይኽ እንኳ እውነት ቢሆን እነርሱን የሚመለከቱትንና በአጠገባቸው የሚዘሉትን አስመልክቶ ግን ማረጋገጫ ሊሰጡ አይችሉም፡፡ #እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ፡፡; 1ኛ ቆሮ 10፡32፡፡ እንዳለው ለማንም የማሰናከያ ድንጋይ አንሁን፡፡

- ጌታችን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ቢሆን ይኽን ያደርግ ይሆን? ራሳችንን እንጠይቅ

- ቅዱስ ጴጥሮስና ሐዋርያት #ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል፡፡ ; የሐ. ሥራ 5፡29፡፡ እንዳሉን ለሠርግም በቤተክርስቲያን የነበረውን ሁሉ በመርሳት ስንወጣ እግዚአብሔርንና ራሳችንን ማክበርን መርሳታችን እጅግ ያስገርማል፡፡ ጌታችን በሠርጉ ቢገኝ ያደረግነውን ያደርጋል፤ ባለበትስ ተጋባዦቹ ሁሉ ይደንሱ ይሆን?

- ጌታችን ምሉዕ በኩለሄ ስለሆነ በሁሉም ሥፍራ ይገኛልና ሁልጊዜ ከሰው ፈቃድ የእርሱን በማስቀደም በአግባብ እንኑር፡፡

# ዘፈንና ዳንስ በመጽሐፍ ቅዱስ የቀጠለ...

- ክርስቲያኖች ከሆንን በነገር ሁሉ ጌታችንን መምሰል አለብን። ማቴ 11:29። ጌታችን አሁን ቀድሞ በሥጋ እንደተገለጠ በመካከላችን ቢሆን እንዘፍናለን፤ እንደንሳለን?

- ጭፈራና ዳንስ ሥጋዊ ደስታን የምንገልጽበት መንገድ ነው።

- ቅዱስ ዮሐንስ ግን #ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።; 1ኛ ዮሐ 2:15 -17። እንዳለን ክርስቲያኖች የዓለም ከሆነው ይልቅ እርሱ በሚወደውና በመረጠው መንገድ ከብረን መኖር ይጠበቅብናል።

# *ትንቢተ ዳንኤል 3 * 1 - 12*

- ናቡከደነፆር ኃይለኛ የባቢሎን ንጉሥ ነበር፡፡ በዘመኑ ብዙ መንግሥታትን በመውጋት በግዛቱ ሥር እንዲተዳደሩ አስገድዶአቸው ነበር፡፡

- ናቡከደነፆር የተቃወሙትን ሁሉ የማይምር ጨካኝና ርኅራኄ የሌለው ንጉሥ ነበር፡፡

- 9 ጫማ የሚረዝም ምስል አሰርቶ ይሰግድና ያሰግድ ነበር፡፡

- ሕዝቡ የዘፈንም ድምጽ ሲሰማ ከሶስቱ ወጣቶች በቀር ለተሰራው ምስል በመስገድ ያመልኩት ነበር፡፡

- ከለዳውያንም ቀርበው ያልሰገዱትን ከሰሱ፡፡ ዳንኤል 3፥8

- ለጣዖት አንሰግድም አናመልከውምም ያሉት ሶስቱ ወጣቶች ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ አብደናጎ ይባሉ ነበር፡፡ ዳንኤል 3፥12

## ሶስቱ ወጣቶች አንሰግድም ያሉት ለምን ነበር?

- ሦስቱ ወጣቶች በባቢሎን ቤተመንግሥት ለታላቅ ሹመት ታጭተው ነበር።

- እግዚአብሔር ታላቅ ሥራ እንድንሠራ ሲመርጠን በዚህ የሚቀኑ ጥቂት ሰዎች የሚኖሩ መሆናቸውንና እነርሱም ወደኋላ ሊስቡ የሚሞክሩ መሆናቸውን ያስረዳል።

- ይኸ ብቻ ሳይሆን በአንድ የተሳሳተ ጉዳይ ላይ አቋም ስንይዝ በሐሰት የሚናገሩብን፤ ስማችንን የሚያጠፉ፤ የሚከሱንና የሚያንገላቱን፤ ክብራችንንና ዝናችንን የሚያጠፉ ሰዎች እንደሚኖሩም የሚያሳስበን ነው።

- ሦስቱም ወጣቶች የገጠማቸው ይኸው ነው። ናቡከደነፆር ላቆመው ምስል አንሰግድም በማለት በተሳሳተው አካሄድ የተነሳ አቋም ስለያዙ ችግር ገጠማቸው። በተጨማሪም ዘፈኑን ሰምተው ብዙውን ሕዝብ ባለመከተላቸው መከሰሳቸውን እንመለከታለን።

- ከለዳውያን ብዙው ሕዝብ ያደረገውን ወጣቶቹ መከተል እንደነበረባቸው አሰቡ። ነገር ግን ይህ አካሄድ ትክክል አይደለም።

# <u>የቀጠለ...</u>

- በርካታ ሰዎች ሴቶችን (B-word, or the H- word) ስለጠሩ፤ ሰዎች በውስጥ ቁምጣቸው ስለሄዱ፤ የውስጥ ቁምጣቸውንም የሚያሳይ አጭር ካናቴራ ለባሽ ስለሆኑ ብዙዎችም ስለተቀበሉት ድርጊቱ ትክክል ነው ወደ ሚል ድምዳሜ አንደርስም፡፡

- በቀላሉ ዝም ብለን የማናደርጋቸው ነገሮች አሉ፡ ምክንያቱም ትክክል አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ደስ ስለማያሰኝ ነው፡፡

- ወጣቶቹ ያልዘፈኑት ዘፈኑ ጣእም የሌለው ስለሆነ፤ ለመደነስ ወይም ለመጨፈር የሚያስችል ጤንነት የጎደላቸው፤ ስለ ሙዚቃም የማያውቁና ያልሰሙ ሆነው ... አይደለም፡፡ ከሁሉ በላይ ዘፈኑ ሕዝቡ ለጣዖት እንዲሰግድ እንደ ምልክት/መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል ስለነበረ ነው፡፡

- የዘፈኑ ዜማ ለጣዖት የመገዛትን መልዕክት የሚያስተላልፍ፤ የእግዚአብሔር ለሆኑ መጥፎ ስሜትን ስለሚፈጥር ነው፡፡

- ከጋብቻ በፊት ለሚፈጸም ግኑኝነት የሚያነሳሱ፤ ተቀባይነት ካለው አኗኗር ወጣ ያለ አካሄድን የሚያመላክቱ፤ አለባበሳቸው ትክክለኛ አይደለም ያሉትን ሰዎችን መግደልን የሚያበረታቱ፤ እንደ ወላጆቻችን፡ መምህራን ያሉ ልንታዘዝላቸው የሚገቡንን መናቅን፤ አደገኛ ዕፅ ተጠቃሚ መሆንንና ማዘዋወርን፤ ትምህርት ማቋረጥን፤ ወደ ኃጢአት የሚገፉ እነዚህ ሙዚቃዎች ዛሬ እጅግ በዝተዋል፡፡

# የቀጠለ...

- በባቢሎን እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቤተ መቅደስ ባይኖራቸውም #ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።፡; ምሳሌ 22*6 #ጕልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው።፡; መዝሙር 119*9 እንደተባለው በልጅነታቸው እግዚአብሔርን ስለውት ነበር።

- ወደ የትም ብንሄድ፤ የትም ብንኖር፤ የምንሠራበት ቦታ ስለ እግዚአብሔር መናገርን የሚገድብ ቢሆን፤ #አንተ እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።፡; መዝ. 119*11 እንዳለው እግዚአብሔርን በሕይወታችን መስበክ ግን እንችላለን።

- ዘጸአት 20*1-6 ፣ ዘሌዋውያን 26*1 ፣ መዝሙር 100*3 ፣ ኤሳይያስ 42*8

- #እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜ ይህ ነው ክብሬን ለሌላ፥ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም።፡; ኢሳይያስ 40*18 ፣ ኢሳይያስ 42*8 እንዳለ ላም አረንጓዴ ሳር ግጣ ነጭ ወተት ቢጫ ቅቤና አይብ እንድትሰጥ ያደረገ እርሱ ብቻ ነው። አህያዋ እንድትናገር፤ ወጣቶቹ ሳይቃጠሉ በእሳት ውስጥ እንዲራመዱ ያደረገ፤ ባሕር ከፍሎ ያሻገረ፤ ከዓለት ውሃ ያፈለቀ፤ ሕሙማንን የፈወሰ፤ ሙታንን ያስነሳ፤ የእውራንን ዓይን ያበራ፤ ጎባጣውን ያቀና፤ ደንቆሮችን ያናገረ፤ አጋንንትን ያወጣ፤ 5000 ሕዝብ በሁለት ዓሳና በአምስት እንጀራ ያጠገበ ... ይቀጥላል እግዚአብሔር ብቻ ነው። ልንሰግለት፤ ልናመልከው፤ ልንዘምርለትና ልናሸበሽብለት የሚገባን እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

-

## የቀጠለ...

- ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት በቴሌቪዥን አገልግሎት፤ በኢንተርኔት፤ በiPod እና በMP3 ማጫወቻዎች መበራከት የተነሳ ሙዚቃ የዓለማችን ሕይወት ትልቁ አካልና በቀላሉም የሚገኝ ለመሆን እየቻለ ነው፡፡

- ዛሬ በርካታ ሰዎች የሚያንቀላፉትና የሚነቁት በሙዚቃ ነው፡፡ በየስፓርት ቤቶች፤ ስንሮጥ፤ የቤት ሥራ ስንሠራ፤ ቪዲዮ ጌሞች በመጫወት ... ክፉውን ሮክና ሮልን ሙዚቃ በአንድም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንገናኘዋለን፡፡

- መኪናችን ያለሬድዮና ሲዲ ማጫወቻ ሆኖ የሚያገኝበትም አጋጣሚ ጠባብ ነው፡፡

- ኤፌሶን 5 5*1-11 የተጻፈው ሙዚቃን እንዴት መመልከት እንዳለብንም የሚያስተምረን ነው፡፡ የዛሬዋ ዓለም ሙዚቃ ወደ እግዚአብሔር የሚስብ የሚያቀርብ ከኃጢአት የሚያርቅ ነው? ውዝዋዜውስ በጽድቅ ላልታነጸው እናሽንፍሃለን እያልን እየታገልነው ላልነው ሰውነታችን መታነጽ ምንጭ ይሆናል? 2ኛ ተሰ. 2፡15፤ 1ኛ ዮሐ 4፡1፤ ኢሳ 23፤16፡ 51፡3፤ ኤፌ 5፡19፤ ዘጸአት 32፡7-18
- ስለዚህ፡- ሙዚቃ ከነጉዳቱ ምን እንደሆነ መርምሩ? የዘፋኞቹን ምሳሌነት ለይታችሁ እወቁና... በማዳመጥ ወይም ባለማዳመጣችሁ ላይ ወስኑ፤ የሚያዝናና ወይስ የሚጎዳ ብላችሁም መርምሩ፤ ...
- በርካታ ምዕራባውያን የሮክ... ሙዚቃ መጥፎ ማኅበራዊ ገጽታዎች እንዳሉትና ወደ አመጽ እና ወንጀለኛነት እንደሚመራ ይስማማሉና ከሁሉ ራሳችንን እንጠብቅ፡፡

ወስብሐት

ለእግዚአብሔር።